
# የኢትዮጵያ የምግብ፣መድሀኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን



# የዜጎች ቻርተር

# ጥር 2008 ዓም

# አዲስ አበባ

የባለስልጣን መስሪያቤታችን መልእክት.........................................Error! Bookmark not defined.
የሰነዱ አጠቃቀም ---------------------------------------------------------------------------------------------------3

1. ስለ ባለስልጣን መስሪያቤታችን ........................................................................................... 3
1.1 ራእያችን ...................................................................................................... 3
1.2 ተልእኳችን .................................................................................................... 3
1.3 የተkkምንበት ዓላማ ......................................................................................... 3
1.4 እሴቶቻችን .................................................................................................... 4
1.5 የመዋቅራችን አደረጃጀት .................................................................................... 4
2. ተገልጋዮቻችን፣ አጋርና ባለድርሻ አካላት ........................................................................... 5
2.1 ተገልጋዮቻችን ................................................................................................ 5
2.2 ባለድርሻ አካላት .............................................................................................. 5
2.3 አጋር ድርጅቶች .............................................................................................. 6
3. የአገልግሎታችን ተጠቃሚዎች ............................................................................................. 6
4. የተገልጋዮቻችን መብትና ግዴታ ........................................................................................... 6
4.1 የተገልጋዮቻችን ግዴታ ...................................................................................... 6
4.2 የተገልጋዮቻችን መብት ...................................................................................... 6
5. የምንሰጣቸው አገልግሎቶች ................................................................................................ 7
5.1የምግብ፣ መድሀኒት፣ ህክምና መሳርያ፣ የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶችና ኮስሞቲክስ ምርቶች ምዝገባና የገበያ ፈቃድ መሰጠት ........................................................................................................ 7
5.2 ለምግብና መድሀኒት ንግድና የጤና አገልግሎት ሰጪ ተkማት ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት ........................................................................................................ 13
5.3 የጤና ባለሙያዎች ሙያ ምዝገባና ፈቃድ መሰጠት ........................................................ 17
5.4 የምግብና መድሀኒት ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ማካሄድ .................................................. 20
5.5 በመግቢያና መውጫ ኬላዎች የመልቀቅያ ፈቃድ መስጠት ................................................. 21
5.6 አገልግሎት ላይ የማይውሉ ምርቶች በአግባቡ መወገዳቸውን ማረጋገጥ ................................... 26
5.7 የመረጃ አቅርቦት ጥያቄ ምላሽ መስጠት ...................................................................... 27
5.8 ከህብረተሰቡና ሌሎች አካላት የሚመጡ ጥቆማዎች ምላሽ መስጠት ....................................... 28
5.9 ከተገልጋዮችና አገልግሎት ተጠቃሚ አካላት የሚነሳ ቅሬታ ምላሽ መስጠት ............................ 29
6. የቅሬታ አቀራረብና ግብረመልስ አሰጣጥ ስርዓታችን ............................................................... 30
7. ተጨማሪ የመረጃ ምንጮቻችን ........................................................................................... 31
8. የተkሙ የበላይ ሀላፊዎችና የአገልግሎት መስጫ ቦታዎች አድራሻ ............................................. 31

9. የዋናው መስሪያቤታችን ፣ቅርንጫፍ ፅህፈትቤቶቻችንና የመውጫና መግቢያ ኬላዎቻችን አድራሻዎች ........ 32
10. የአገልግሎት መጠየቂያ ማመልከቻ ቅፆች ........ 34

## የዜጎች ቻርተር ሰነዱ አጠቃቀም

ይህ የዜጎች ቻርተር ሰነድ ባለስልጣን መስሪያቤታችን በአዋጅ ቁጥር 661/2002 በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት ለተገልጋዮቻችንና ለህብረተሰቡ የምንሰጣቸው አገልግሎቶች ዝርዝር፣ የአገልግሎት መስጫ ቦታዎች፣ አገልግሎቱ ለመስጠት ተገልጋዮቻችን ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶችና አገልግሎቱ ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ እንዲሁምበገባነው ቃል መሰረት ለተገልጋዮቻችንአገልግሎቱ ሳንሰጥ ስንቀር ወይም በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደታችን ማንኛውም ዓይነት ቅሬታ ሲኖራቸው ቅሬታ የሚያቀርቡበትና የግብረ መልስ አሰጣጥ ስርዓታችን እና ሌሎች ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች የያዘ ማንዋል ነው፡፡ ይህም የመስሪያቤታችን አሰራር ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ለማስኬድና መልካም አስተዳደር ከማስፈን አንፃር ጉልህ ሚና ይጫወታል ብለን እናምለን፡፡

በዚህ መሰረት ማንዋሉ ለአጠቃቀም ቀላል እንዲሆን ተደርጎ የተዘጋጀ ሲሆን በበለጠ ግልፅነት ለመፍጠር የሚከተሉት መረጃዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

- ተገልጋዮች ለእያንዳንዱ አገልግሎት ለመጠየቅ መሙላት ያለባቸው የማመልከቻ ቅፆች በሰነዱ መጨረሻ ላይ ተያይዘዋል፡፡ ስለሆነም ተገልጋዮች ለሚፈልጉት አገልግሎት ለመጠየቅ የማመልከቻ ቅፁ በሞሙላትና ሌሎች መስፈርቶች በማያያዝ ማቅረብ ይኖርባችዋል፡፡
- ተገልጋዮች አገልግሎት ለማግኘት ማማላት ያለባቸው መስፈርቶች በአገልግሎቱ መጨረሻ ኮለመን የተጠቀሱ እንደተጠበቀ ሁኖ በእያንዳንዱ የቁጥጥር መመርያዎች በጥልቀት በማንበብ በመመርያው ላይ የተጠቀሱ ተጨማሪ መስፈርቶች ማማላት ይኖርባችዋል፡፡ መመርያዎቹም ከባለስልጣን መስሪያቤቱ ድህረ ገፅ ማግኘት ይቻላል፡፡
- ለእያንዳንዱ አገልግሎት ለማግኘት የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ በዝርዝር የተጠቀሱ እንደተጠበቁ ሁኖው በሚንስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 370/2008 ላይ የምግብ፣መድህኒት፣ የጤና ተkማትና የጤና ባለሙያዎች ምዝገበና ፈቃድ አሰጣጥ አገልግሎት ክፍያ ተመንን ለመወሰን የወጣ ደንብ በጥልቀት ማየት ያስፈልጋል፡፡

ተገልጋዮች በተጠቀሰው ጊዜ ገደብና የጥራት ደረጃ አገልግሎት ለማግኘት ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች በሙሉ አሟልተው መገኘት ይኖርባችዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎት የሚሰጠው የስራ ክፍል በተቀመጠው የጊዜ ገደብ አገልግሎቱ ያልሰጠ እንደሆነ ተገልጋዮች በተቀመጠው የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት መሰረት ቅሬታቸው በየደረጃው ላለው አካል ማቅረብ

ይችላሉ፡፡ ቅሬታ የቀረበለት የስራ ሀላፊም በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ተገቢ ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

# 1. ስለ ባለስልጣን መስሪያቤታችን

## 1.1 ራእያችን

ጥራት ያለው የጤና አገልግሎትና ግብዓት ለሁሉም ዜጎች፡፡

## 1.2 ተልእኳችን

የምግብ፣የመድሀኒትና የጤና ተቋማትና የጤና ባለሙያዎችን የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት እና በመቆጣጠር ፤በምዝገባና በጥራት ምርመራ ግብአቶችን ጥራት ደህንነት እና ፈዋሽነት በማረጋገጥ እንዲሁም አግባባዊ አጠቃቀምን በማስፈን እና ወቅታዊ መረጃዎችን በማቅረብ የህብረተሰቡን ጤና መጠበቅ ነው፡፡

## 1.3 የተkkምንበት ዓላማ

ባለስልጣን መስሪያቤታችን ሲkkም የሚከተሉትን ዓላማዎች መሰረት በማድረግ ነው፡፡

- ☞ ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚውሉ ምግቦች ጥራትና ደህንነት የተጠበቀ መሆኑ ማረጋገጥ፣
- ☞ ህብረተሰቡ የሚኖርበት አከባቢ ለጤና ተስማሚ መሆኑ ማረጋገጥ፣
- ☞ ህብረተሰቡ በተለያየ ምክንያት ጤናውን ሲታወክ የሚታከምበትን ጤና ተkም ደረጃውን የጠበቀ መሆኑና የሚያክመውን ባለሙያም ሙያዊ ብቃትና ስነ ምግባር ያለው መሆኑ የማረጋገጥ እና
- ☞ ታካሚዎች ከህመማቸው ለመፈወስ ወይም ህብረተሰቡ ከበሽታን ለመከላከል የሚወስደውን መድሀኒት ጥራት፣ ደህንነት፣ፈዋሽነትና አግባባዊ አጠቃቀምን የማረጋገጥና

ከጥራትና ደህንነት ጉድለት ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ የጤና ችግሮች የመጠበቅ ስራዎችን ለማከናወን ነው፡፡

## 1.4 እሴቶቻችን

ከህብረተሰቡንና ከመንግስት የተሰጠንን ሀላፊነትና ተልእኮ ስንፈፅም የሚከተሉትን መሰረታዊ እሴቶች ባከበረና በተከተለ መንገድ ይሆናል፡፡

1. **ግልፅነት**፡- አመራሩና ሠራተኞች ግልፅነት የተሞላበትን አሠራርና ውሳኔ ሰጪነት በማጠናከር የዘርፉን ራዕይና ተልእኮ ለማሳካት የግልፅነት መርህን ተከትለን እንሰራለን፡፡
2. **ታማኝነት፡-** ከህዝብና ከመንግስት የተሰጠን ስራና ሀላፊነት ባለማጓደል የዘርፉን ተልእኮ ለማሳካት እንሰራለን፡፡
3. **ሙያተኛነት፡-** ዘርፉ የሚጠይቀውን ሙያዊ ብቃትና ስነ ምግባር በመላበስ የተቀመጠውን ራዕይና ተልዕኮ እናሳካለን፡፡
4. **ጥራት ተኮር** ፡- በጤና አገልግሎቶችና ግብዓቶች ጥራት መጓደል አንደራደርም፡፡
5. **የህዝብ ጥቅም ማስቀደም** ፡- ተግባራችን ሁሉ የህዝብ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥና ህብረተሰቡ በተሻለ ሊጠቀም የሚችልበትን ሁኔታ በማመቻቸት የህዝብን ጥቅም እናስቀድማለን፣
6. **ለለውጥ ዝግጁነት** ፡- አመራሩና ሰራተኛው የአገልጋይነት መንፈስን በማዳበር ለውጥን በፍጥነት ተቀብሎ የመስራትና የመምራት አቅምን በማጎልበት ከሚመጣው ለውጥ ሊገኝ የሚችለውን መልካም አጋጣሚ አሟጦ ለመጠቀም እንዲቻል ከለውጥ ጋር አብሮ ለመሄድ ተግተን እንሰራለን፡፡
7. **ተጠያቂነት**፡-ሀላፊነታችን ከተጠያቂነት ጋር በመቀበል የኪራይ ሰብሳቢትን አመለካከትና ተግባር ከመሠረቱ በመናድና ተጠያቂነትን የተቀበለ የልማት ሰራዊት በመፍጠር የቁጥጥር ስራውን ውጤታማ እናደርጋለን፡፡
8. **ምስጢር ጠባቂነት**፡- ማንኛውም የዘርፉ አመራርና ሰራተኛ በግልም ሆነ በቡድን የመ/ቤቱንና ተገልጋዮቻችን ምስጢሮች በመጠበቅ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳያገኝ ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ ያለመስጠት አሰራርን እንከተላለን፡፡

## 1.5የመዋቅራችን አደረጃጀት

ባለስልጣን መሰሪያቤታችን የተሰጠንን ሀላፊነት ለመፈፀም በዋናው መስሪያቤት፣ 7 ቅርንጫፍ ፅህፈትቤቶችና 17 የመውጫና መግቢያ ኬላዎች አደረጃጀት በመፍጠር አገልግሎቱ በመስጠት

ላይ ይገኛል፡፡ አገልግሎቱን የተሳለጠ ለማድረግ በስሩ ከ20 በላይ የተለያዩ ቴክኒካል ዳይሬክቶሬቶችናድጋፍ ሰጪ የስራ ክፍሎች ይገኛሉ፡፡

## 2. ተገልጋዮቻችን፣አጋርና ባለድርሻ አካላት

### 2.1 ተገልጋዮቻችን

ባለስልጣን መስሪያቤታችን በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለህብረተሰቡ በምንሰጣቸው አገልግሎቶች ላይ የሚከተሉት ዋና ዋና ተገልጋቻችን ናቸው፡፡

- የምግብ አምራች፣አስመጪ፣ላኪና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች
- የመድሀኒት፣ህክምናመመገልገያ መሳርያዎችና የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶች አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች
- የኮስሞቲክስ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች
- ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች
- ልዩ የጤና ማእከላት
- ጠቅላላና ስፔሻሊስት ሀኪሞች፣አዋላጅ ነርሶች፣ ከውጭ ሀገር የሚመጡ ጤና ባለሙያዎች
- የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተkማት

### 2.2 ባለድርሻ አካላት

የሚከተሉት ሴክተር መስሪያቤቶች በምናከናውናችው የቁጥጥር ስራዎቻችን ባለድርሻ አካላት ሆኖው ከኛ ጋር በቅንጅት አብረውን የሚሰሩና ተልእኳችን ከመፈፀም አንፃር ጉልህ ሚና የሚጫወቱ ተkማት ናቸው፡፡

- ንግድ ሚንስቴር
- የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን
- ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
- የምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት
- የወተትና ስጋ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት
- የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ደርጅት
- የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ
- የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
- ከፍተኛ የምግብና ጤና ትምህርት ተkማት

☞ መከላከያ ሰራዊትና ፌዴራል ፖሊስ እና ሌሎች

## 2.3 አጋር ድርጅቶች

የህብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ በምናከናውናቸው የቁጥጥር ስራዎች እንደ WHO, UNICEF, UNFPA, USP/PQM, USAID, gain, FAO እና የመሳሰሉ መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች የተለያዩ ቴክኒካዊና ፋይናንሻዊ ድጋፎች በማድረግ አብረውን እየሰሩ ያሉ ተkማት ናቸው፡፡

# 3. የአገልግሎታችን ተጠቃሚዎች

አጠቃላይ በምንሰጣቸው አገልግሎቶች ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች በዘርፉ የተሰማሩ ተkማትና ባለሙያዎች ሲሆኑ ከራእይና ተልእኳችን መረዳት እንደሚቻለው አጠቃላይ የምናከናውናቸው የቁጥጥር ስራዎች ህብረተሰቡ የጥራትና ደህንነት ከጎደለው ምግብና መድሀኒት እንዲሁም ጤና አገልግሎት ጋር ተያይዞ የሚመጡ የጤና ችግሮች መጠበቅ እንደመሆኑ መጠን አጠቃላይ ህብረተሰቡ ተጠቃሚ ነው፡፡

# 4. የተገልጋዮቻችን መብትና ግዴታ

## 4.1 የተገልጋዮቻችን ግዴታ

ተገልጋዮቻችን ከባለስልጣን መስሪያቤቱ አገልግሎት ለማግኘት የባለሰልጣን መስሪያቤቱ ህግና አሰራር የመከተል፣ መመርያን የማክበርና ለእያንዳንዱ አገልግሎት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች አሟልቶ የመገኘትና የአገልግሎት ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡

## 4.2 የተገልጋዮቻችን መብት

ተገልጋዮቻችን በዚህ ቻርተር ውስጥ ከተካተቱ አገልግሎቶች ውስጥ የሚፈልጉትን አገልግሎትና መረጃ ከባለስልጣን መስሪያቤቱ ዋናው መስሪያቤት፣ቅርንጫፍ ፅህፈትቤትና የመውጫና መግቢያ ኬላዎች ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብና የጥራት ደረጃ

የማግኘት፣ማብራርያ የመጠየቅ፣በቂ ምላሽ የማግኘት፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ሂስ የመስጠት፣ ቅሬታቸው የመደመጥና ግብረመልስ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

# 5. የምንሰጣቸው አገልግሎቶች

## 5.1 የምግብ፣ መድሀኒት፣ ህክምና መሳርያ፣ የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶችና ኮስሞቲክስ ምርቶች ምዝገባና የገበያ ፈቃድ መሰጠት


### 5.1.1 የአገልግሎቱ መግለጫ

ይህ አገልግሎት በባለስልጣን መስሪያቤቱ ቁጥጥር የሚካሄድባቸውና እንዲመዘገቡ ተብለው የተለዩ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የሚመረቱ ምግቦች፣ዘመናዊና ባህላዊ መድሀኒቶች፣የህክምና መገልገያዎችና መሳርያዎች፣የላቦራቶሪ ኬሚካሎችና ሪኤጀንቶች፣ኮስሞቲክሶች እና ሌሎች ምርቶች ተገቢው የጥራትና ደህንነት መስፈርቶች ማሟላተቸውን በማረጋገጥ የመመዝገብና ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንዲውሉ የገበያ ፈቃድ የመሰጠት አገልገሎት ይሰጣል፡፡

የምርቶቹ ጥራትና ደህንነት ለማረጋገጥ በዋናነት ሶስት መሰረታዊ ስራዎች የሚከናወኑ ሲሆን እነሱም ስለ ምርቶቹ አመራረት ሂደት፣ይዘትና የጥራት ማረጋገጥ ስርዓት በተመለከተ የሚገልፁ ሰነዶች የመገምገም፣ምርቶቹ የመልካም አመራረት ስርዓት ተከትለው የሚመረቱ ስለመሆናቸው በኢንስፔክሽን የማረጋገጥና የምርቶቹ ናሙና በመውሰድ በላቦራቶሪ እንዲመረመሩ በማድረግ ጥራታቸውና ደህንነታቸው የማረጋገጥ ስራዎች ይከናወናል፡፡

አገልግሎቱ ለማግኘት ጥያቄ የሚቀርብበትም ሆነ ምላሽ የሚሰጥበት በደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ይሆናል፡፡

### 5.1.2 የአገልገሎት አሰጣጥ ሂደት



## 5.1.3 አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ፣ የሚፈጀው ጊዜና ተገልጋዮች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

| ተቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱ ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ | የአገልግሎት ክፍያ | አገልግሎቱ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የምግብ ምዝገባና የገበያ ፈቃድ መስጠት | | | | |
| 1.1 | አዲስ የምግብ ምዝገባና የገበያ ፈቃድ መስጠት | በዋናው መስሪያቤት | | | |
| | ▪ የሀገር ውሰጥ ምግብ | " | 17 ቀን6 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | | <u>አዲስ ምዝገባ ለማካሄድ</u><br>- የተሟላ ማመልከቻ<br>- የምግቡ አመራረት ሂደት፣ይዘት፣የጥራት ማረጋገጥ ስርዓት እና የመሳሰሉ መረጃዎች የያዘ ሰነድ (Dossier)<br>- ለምርቱ ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ አገልግሎት የሚውል test method & Reference standard<br><br><u>ዳግም ምዝገባ ለማካሄድ</u><br>- በነባሩ የተመዘገበ ምግብ የአመራረት ሂደት፣ ይዘት፣ የምርመራ ዘዴ እና ሌሎች በምርቱ ላይ የተደረጉ ለውጦች አለመኖራቸው የሚገልጽ ዳብዳቤ<br>- አመታዊ የምግቡ አመራረት ሂደት ግምገማ ሪፖርት<br><br><u>የምርት/አሰራር ለውጥ ለማድረግ</u><br>- የተሟላ ማመልከቻ<br>- የአሰራር ወይም የይዘት ለውጥ የተደረገበት ምግብ ይዘት፣ አመራረት ሂደት፣ የምርመራ ዘዴና ሌሎች መረጃዎች የያዘ ሰነድ<br>- ለምግቡ ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ የሚያስፈልግ test method & Reference standard<br>እና<br>- ሌሎች በምግብ ምዝገባና ፈቃድ ቁጥጥር መመርያዎች ላይ የተገለፁ መስፈርቶች |
| | ▪ የውጭ ሀገር ምግብ | " | 2 ወር 2 ቀን 6 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | 1650 | |
| 1.2 | ዳግም የምግብ ምዝገባ ማካሄድ | " | 1 ቀን 2 ሰዓት ከ15 ደቂቃ | 870 | |
| 1.3 | የምርት ወይም የአሰራር ለውጥ ማድረግ | " | 17 ቀን 6 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | 870 | |

<table>
<tr><td>2.</td><td colspan="5">የመድሀኒት ምዝገባና የገበያ ፈቃድ መስጠት</td></tr>
<tr><td>2.1</td><td colspan="4">በሀገር ውስጥ የተመረተ መድሀኒት ምዝገባ</td><td rowspan="22"><u>አዲስ ምዝገባ ለማካሄድ</u><br><br>- የተሞላ ማመልከቻ<br>- የመድሀኒቱ/ህክምና መሳርያው/ላቦራቶሪ ሪኤጀንት ወይም የኮስሞቲክሱ አመራረት ሂደት፣ይዘት፣የጥራት ማረጋገጥ ስርዓት እና የመሳሰሉ መረጃዎች የያዘ ሰነድ (Dossier) ከነ ሶፍት ኮፒ<br>- ለምርቱ ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ አገልግሎት የሚውል test method & Reference standard<br><br><u>ዳግም ምዝገባ ለማካሄድ</u><br><br>- በነባሩ የተመዘገበ መድሀኒቱ/ህክምና መሳርያ/ላቦራቶሪ ሪኤጀንት ወይም ኮስሞቲክስ የአመራረት ሂደት፣ ይዘት፣ የምርመራ ዘዴ እና ሌሎች በምርቱ ላይ የተደረጉ ለውጦች አለመኖራቸው የሚገልጽ ዳብዳቤ<br>- አመታዊ የምርቱ አመራረት ሂዳት ግምገማ ሪፖርት<br>- ለምርቱ ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ አገልግሎት የሚውል test method & Reference standard<br><br><u>የምርት/አሰራር ለውጥ ለማድረግ</u><br><br>- የተሞላ ማመልከቻ<br>- የአሰራር ወይም የይዘት ለውጥ የተደረገበት መድሀኒቱ/ህክምና መሳርያ/ላቦራቶሪ ሪኤጀንት ወይም ኮስሞቲክስ ይዘት፣ አመራረት ሂደት፣ የምርመራ ዘዴና ሌሎች መረጃዎች የያዘ ሰነድ (Dossier) ከነ ሶፍት ኮፒ<br>- ለምርቱ ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ የሚያስፈልግ test method & Reference standard</td></tr>
<tr><td></td><td>- አዲስ መድሀኒት</td><td>"</td><td>1 ወር 15 ቀን 1 ሰዓት</td><td rowspan="16">የሚንስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 370/2008 በተቀመጠው ተመን መሰረት</td></tr>
<tr><td></td><td>- ዳግም ምዝገባ</td><td>"</td><td>2 ቀን 1 ሰዓት ከ40 ደቂቃ</td></tr>
<tr><td></td><td>- ምርት/አሰራር ለውጥ</td><td>"</td><td>1 ወር 15 ቀን 1 ሰዓት</td></tr>
<tr><td>2.2</td><td colspan="3">ውጭ ሀገር ተመርተው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ መድሀኒቶች ምዝገባ</td></tr>
<tr><td>2.2.1</td><td colspan="3">SRA ባላቸው ሀገራት የሚመረቱ መድሀኒቶች ምዝገባ</td></tr>
<tr><td></td><td>- አዲስ መድሀኒት</td><td>"</td><td>17 ቀን 1 ሰዓት</td></tr>
<tr><td></td><td>- ዳግም ምዝገባ</td><td>"</td><td>2 ቀን 1 ሰዓት ከ40 ደቂቃ</td></tr>
<tr><td></td><td>- ምርት/አሰራር ለውጥ</td><td>"</td><td>17 ቀን 1 ሰዓት</td></tr>
<tr><td>2.2.2</td><td colspan="3">SRA በሌላቸው ሀገራት የሚመረቱ መድሀኒቶች ምዝገባ</td></tr>
<tr><td></td><td>- አዲስ መድሀኒት</td><td>"</td><td>3 ወር 5 ቀን 1 ሰዓት</td></tr>
<tr><td></td><td>- ዳግም ምዝገባ</td><td>"</td><td>2 ቀን 1 ሰዓት ከ40 ደቂቃ</td></tr>
<tr><td></td><td>- ምርት/አሰራር ለውጥ</td><td>"</td><td>3 ወር 5 ቀን 1 ሰዓት</td></tr>
<tr><td>2.2.3</td><td colspan="3">በልዩ ሁኔታ በአስቸኳይ ጊዜ (Fast truck) መድሀኒት ምዝገባ</td></tr>
<tr><td></td><td>- አዲስ መድሀኒት</td><td>"</td><td>2 ወር 10 ቀን 1 ሰዓት</td></tr>
<tr><td></td><td>- ዳግም ምዝገባ</td><td>"</td><td>2 ቀን 1 ሰዓት ከ40 ደቂቃ</td></tr>
<tr><td></td><td>- ምርት/አሰራር ለውጥ</td><td>"</td><td>2 ወር 10 ቀን 1 ሰዓት</td></tr>
<tr><td>3.</td><td colspan="3">የህክምና መሳርያዎች ምዝገባና የገበያ ፈቃድ መስጠት</td><td></td></tr>
<tr><td>3.1</td><td>በመደበኛ አሰራር ህክምና መሳርያዎች ምዝገባ</td><td>"</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td></td><td>- አዲስ ህክምና መሳርያ</td><td>"</td><td>17 ቀን 2 ሰዓት ከ20 ደቂቃ</td><td>1650</td></tr>
<tr><td></td><td>- ዳግም ምዝገባ</td><td>"</td><td>2 ቀን 2 ሰዓት ከ15 ደቂቃ</td><td>870</td></tr>
<tr><td></td><td>- ምርት/አሰራር ለውጥ</td><td>"</td><td>17 ቀን 2 ሰዓት</td><td>1300</td></tr>
</table>

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከ20 ደቂቃ | | እና<br><br>- ሌሎች በመድሀኒት፣ህክምና መሳርያና ኮስሞቲክስ ምዝገባና ፈቃድ ቁጥጥር መመርያዎች ላይ የተገለፁ መስፈርቶች |
| 3.2 | በልዩ ሁኔታ በአስቸኳይ ጊዜ (Fast truck) የህክምና መሳርያዎች ምዝገባ | " | | | |
| | - አዲስ ህክምና መሳርያ | " | 5ቀን 2 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | 1650 | |
| | - ዳግም ምዝገባ | " | 2 ቀን 2 ሰዓት ከ15 ደቂቃ | 870 | |
| | - ምርት/አሰራር ለውጥ | " | 5 ቀን 2 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | 1300 | |
| 4. | **የላቦራቶሪ ኬሚካሎችና ሪኤጀንቶች ምዝገባና የገበያ ፈቃድ መስጠት** | | | | |
| 4.1 | በመደበኛ አሰራር የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶች ምዝገባ | " | | | |
| | - አዲስ የላቦራቶሪ ኬሚካሎችና ሪኤጀንቶች | " | 17 ቀን 2 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | 1650 | |
| | - ዳግም ምዝገባ | " | 2 ቀን 2 ሰዓት ከ15 ደቂቃ | 870 | |
| | - ምርት/አሰራር ለውጥ | " | 17 ቀን 2 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | 1300 | |
| 4.2 | በልዩ ሁኔታ በአስቸኳይ ጊዜ (Fast truck) የላባራሪ ሪኤጀንቶች ምዝገባ | " | | | |
| | - አዲስ የላቦራቶሪ ኬሚካሎችና ሪኤጀንቶች | " | 5 ቀን 2 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | 1650 | |
| | - ዳግም ምዝገባ | " | 1 ቀን 2 ሰዓት ከ15 ደቂቃ | 870 | |
| | - ምርት/አሰራር ለውጥ | " | 5 ቀን 2 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | 1300 | |
| 5. | **የመድሀኒት ይዘት ያላቸው ውበት መጠበቂያ ምርቶች ምዝገባና የገበያ ፈቃድ መስጠት** | | | | |
| | - አዲስ ምርት ምዝገባ | " | 1 ወር 5 ቀን 2 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | 1650 | |
| | - ዳግም ምዝገባ | " | 4 ቀን 1 ሰዓት ከ15 ደቂቃ | 870 | |
| | - ምርት/አሰራር ለውጥ | " | 1 ወር 5 ቀን 2 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | 1300 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 6. | **ባህላዊ መድሀኒት ምዝገባና የገበያ ፈቃድ መስጠት** | | | | |
| | - አዲስ ምርት ምዝገባ | " | 7 ቀን 1 ሰዓት ከ30 ደቂቃ | | *<u>አዲስ ምዝገባ ለማካሄድ</u>*<br>- የተሟላ ማመልከቻ<br>- የባህላዊ መድሀኒቱ አመራረት ሂደት፣ይዘት፣የጥራት ማረጋገጥ ስርዓት እና የመሳሰሉ መረጃዎች የያዘ ሰነድ (Dossier) ከነ ሶፍት ኮፒ<br>- ለምርቱ ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ አገልግሎት የሚውል test method & Reference standard<br>*<u>ዳግም ምዝገባ ለማካሄድ</u>*<br>- በነባሩ የተመዘገበ ባህላዊ መድሀኒት የአመራረት ሂደት፣ ይዘት፣ የምርመራ ዘዴ እና ሌሎች በምርቱ ላይ የተደረጉ ለውጦች አለመኖራቸው የሚገልጽ ዳብዳቤ<br>- አመታዊ የባህላዊ መድኃኒቱ አመራራት ሂዳት ግምገማ ሪፖርት<br>*<u>የምርት/አሰራር ለውጥ ለማካሄድ</u>*<br>- የተሟላ ማመልከቻ<br>- የአሰራር ወይም የይዘት ለውጥ የተደረገበት ባህላዊ መድሀኒት ይዘት፣ አመራረት ሂደት፣ የምርመራ ዘዴና ሌሎች መረጃዎች የያዘ ሰነድ (Dossier) ከነ ሶፍት ኮፒ<br>- ለምርቱ ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ የሚያስፈልግ test method & Reference standard<br>እና<br>- ሌሎች በባህላዊ መድሀኒት ምዝገባና ፈቃድ ቁጥጥር መመርያ ላይ የተገለፁ መስፈርቶች |
| | - ዳግም ምዝገባ | " | 2 ቀን 1 ሰዓት ከ50 ደቂቃ | | |
| | - ምርት/አሰራር ለውጥ | " | 7 ቀን 1 ሰዓት ከ30 ደቂቃ | | |
| 7. | የህክምና ሙከራ ፈቃድ መሰጠት | " | 6 ቀን ከ35 ደቂቃ | 2100 | - |
| 8. | የመድሀኒትና የህክምና መሳርያዎች ቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ መስጠት (Pre-Import permit ) | | | | - የተሟላ ማመልከቻ<br>- ወቅታዊ የኢንቨስትመነት ፍቃድ<br>- ከጤ/ጥ ሚ/ር ወይም ከክልል ጤና ቢሮዎች የድጋፍ ደብዳቤ<br>- የምርቱ ሰርተፊኬት ኦፍ ኦርጅን፣ ፕሮፈርማ ኢንቮይስና ፍሪ ሴልስ ሰርተፊኬት<br>ምርቱ ለገበያ ሽያጭ እንደማይውል የሚገልፅ የኮሚትመንት ዳብዳቤ |
| 9. | የውጭ ሀገር መድሀኒት የግዢ ፈቃድ መስጠት (purchase order) | " | 10 ደቂቃ | | - የተሟላ ማመልከቻ<br>- በአራት ኮፒ የተዘጋጀ የምርት ግዢ መጠየቂያ ቅጽ<br>- ፕርፎርማ ኢንቮይስ፣ |
| 10. | የአንድ ግዜ የመድሀኒት ግዢ ፈቃድ መሰጠት | በዋናው መስሪያቤትና በሁሉም | 15 ደቂቃ | | - የተሟላ ማመልከቻ ፤<br>- የጤና ጥበቃ ሚንስቴር፣ የክልል ጤና ቢሮ ወይም ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል የተፃፈ ድጋፍ ደብዳቤ፣ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ቅ/ፅ/ህ/ቤቶች | | | - ምርቱን ለመግዛት የተወከለው ባለሙያ የውክልና ደብዳቤ<br>- ሌሎች በአንድ ግዜ የመድሀኒት ግዢ ፈቃድ አሰጣጥ መመርያ ላይ የተቀመጡ መስፈርቶች |
| 11. | ልዩ የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሀኒቶችና ፕሪከርሰር ኬሚካልስ ግዢ ፈቃድ መስጠት | ዋናው መስሪያቤት | ደቂቃ | | - የተ/ላ ማመልከቻ ፤<br>- የሚገዙ ምርቶች ዝርዝርና ምርቱ ለምን አገልግሎት የሚውል ስለመሆኑ የሚገልፅ ደብዳቤ<br>- ኘሮፎርማ ኢንቮይስ |


## 5.2 ለምግብና መድሀኒት ንግድና የጤና አገልግሎት ሰጪ ተkማት ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት

### 5.2.1 የአገልግሎቱ መግለጫ

ይህ አገልግሎት በምግብ፣መድሀኒት፣ህክምና መሳርያዎችና መገልገያዎች፣ የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶች፣ የውበት መጠበቂያ ምርቶች ማምረት፣ ማስመጣት፣መላክ፣ ጅምላ ማከፋፈል እንዲሁም ጤና አገልግሎት መስጠት ስራዎች የሚሰማሩ ተkማት ምርቱን ወይም አገልሎቱን በተገቢው ሁኔታ ለህብረተሰቡ ለማቅረብ የሚያስችል ሙያዊና ተkማዊ ብቃት ያላቸው ስለመሆኑ በማረጋገጥ የሚሰጥ የስራ ፈቃድ ነው፡፡

የድርጅቶቹ ብቃት ለማረጋገጥ በዋናነት የመስሪያ፣ ማከማቻ ወይም አገልግሎት መስጫ ህንፃ ምርቱንለማምረት፣ ለማከማቸት ወይም አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችል መሆኑ፣ አስፈላጊ መሳርያዎችና ማቴሪያሎች የተሟሉ መሆናቸው እንዲሁም ስራውን የሚያከናውኑ ሰራተኞች አግባብነት ያለው ሙያ ያላቸው መሆኑና ጤናቸው የተጠበቀ ስለመሆኑ የማረጋገጥ እንዲሁም ድርጅቱ ስራውን በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ስራዎች ይከናወናል፡፡

### 5.2.2 የአገልገሎት አሰጣጥ ሂደት



## 5.2.3 አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ፣ የሚፈጀው ጊዜና ተገልጋዮች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

| ተቁ | የሚሰጡ አገልገሎት ዝርዝር | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱ ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ | የአገልግሎት ክፍያ | አገልግሎቱ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የምግብ ተkማት የብቃት ማረጋጫ ምስክር ወረቀት መስጠት | | | | |
| 1.1 | የምግብ አምራች ድርጅቶች | ዋናው መስሪያቤትና በሁሉም ቅርንጫፍ ፅህፈትቤቶች | 1 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | 1150 | *<u>የምግብ፣መድሀኒት፣ህክምና መሳርያዎች፣ የውበትና የንፅህና መጠበቂያ ምርቶች አምራች ድርጅቶች</u>*<br>- የተሞላ ማመልከቻ<br>- የቴክኒካል ባለሙያዎች የትምህርት ማስረጃና የቅጥር ስምምነት ውል<br>- የድርጅቱ የማሽነሪ ኢንስታሌሽን ለይአውት<br>- የድርጅቱ ባለቤት ወይም ስራስከያጅ ሁለት የፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶግራፍ<br>- የቤት ካርታ ኮፒ ወይም በውልና ማስረጃ የተረጋገጠ የቤት ኪራይ ውል<br>- በባለሥልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ በወከለው አካል የተካሄደ የኢንስፔክሽን ሪፖርት<br>- ሌሎች በምግብ፣ መድሀኒት፣ ህክምና መሳርያዎች፣ የውበትና የንፅህና መጠበቂያ ምርቶች  አምራች ድርጅቶች ቁጥጥር መመርያዎች የተጠቀሱ መስፈርቶች<br><br>*የምግብ፣ መድሀኒት፣ ህክምና መሳርያዎች፣ የውበትና የንፅህና መጠበቂያ ምርቶች*<br>*<u>አስመጪ፣አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች</u>*<br>- የተሟላ ማመልከቻ<br>- የቴክኒካል ባለሙያ የትምህርት ማስረጃና የቅጥር ስምምነት ውል<br>- የቤት ካርታ ኮፒ ወይም በውልና ማስረጃ የተረጋገጠ የቤት ኪራይ ውል<br>- የድርጅቱ ባለቤት ወይም ስራአስከያጅ ሁለት ፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶግራፍ<br>- በባለሥልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ በወከለው አካል የተካሄደ የኢንስፔክሽን ሪፖርት<br>- ሌሎች የምግብ፣ መድሀኒት፣ ህክምና መሳርያዎች፣ የውበትና |
| 1.2 | የምግብ አስመጪ፣ላኪና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች | " | 50 ደቂቃ | 650 | |
| 2. | የመድሀኒት፣ህክምና መሳርያዎችና ላቦራቶሪ ሪኤጀንት ተkማት የብቃት ማረጋጫ ምስክር ወረቀት መስጠት | | | | |
| 2.1 | የመድሀኒት፣ህክምና መሳርያዎችና የላቦራቶሪ ኬሚካሎችና ሪኤጀንቶች አምራች ድርጅቶች | ዋናው መስሪያቤት | 10 ቀን ከ40 ደቂቃ | 1150 | |
| 2.2 | የመድሀኒት፣ ህክምና መሳርያዎችና የላቦራቶሪ ኬሚካሎችና ሪኤጀንቶች አስመጪ፣ ላኪና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች | ዋናው መስሪያትና በሁሉም ቅርንጫፍ ፅህፈትቤቶች | 50 ደቂቃ | 650 | |
| 3. | የውበት መጠበቂያ፣የንጽህና መጠበቂያና ዲተርጀንት ምርት ተkማት | | | | |
| 3.1 | የውበት መጠበቂያ ፣የንፅህና መጠበቂያና ዲተርጀንት ምርቶች አምራች ድርጅቶች | " | 1 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | 1150 | |
| 3.2 | የውበት መጠበቂያ፣የንፅህና መጠበቂያና ዲተርጀንት ምርቶች አስመጪ፣ላኪና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች | " | 50 ደቂቃ | 650 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የንፅህና መጠበቂያ ምርቶችአስመጪ፣አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች ቁጥጥር መመርያዎች የተጠቀሱ መስፈርቶች |
| 4. | የትምባሆ አስመጪና አከፋፋይ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት | " | 50 ደቂቃ | 1300 | - የተሟላ ማመልከቻ፤<br>- የቤት ካርታ ኮፒ ወይም በውልና ማስረጃ የተረጋገጠ የቤት ኪራይ ውል<br>- የድርጅቱ ባለቤት ወይም ስራስከያጅ ሁለት የፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶግራፍ<br>- በባለሥልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ በወከለው አካል የተካሄደ የኢንስፔክሽን ሪፖርት<br>- ሌሎች በትምባሆ ቁጥጥር መመርያ የተጠቀሱ መስፈርቶች |
| 5. | የጤና ተkማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት | | | | |
| | - ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | " | 6 ቀን 1 ሰዓት ከ30 ደቂቃ | 1600 | - የተሟላ ማመልከቻ<br>- የቴክኒክ ባለሙያዎች የትምህርት ማስረጃና የቅጥር ስምምነት ውል<br>- የቤት ካርታ ኮፒ ወይም በውልና ማስረጃ የተረጋገጠ የቤት ኪራይ ውል<br>- የቴክኒካል ባለሙያ ሁለት ፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎችየኢንስፔክሽን ሪፖርት /በባለሥልጣኑ የሚካሄድ<br>- ሌሎች በእያንዳንዱ ጤና ተkም ደረጃ (Standard) ላይ የተቀመጡ መስፈርቶች |
| | - ልዩ የጤና ማእከላት | " | 5 ቀን 1 ሰዓት ከ10 ደቂቃ | 1600 | |
| | - ስፔሻሊቲ ክልኒኮች | " | 7 ቀን 1 ሰዓት ከ30 ደቂቃ | 1600 | |
| 6. | የብቃት ማረጋጫ ምሰክር ወረቀት እድሳት ማድረግ፣ለውጥና ምትክ መስጠት፣ መሰረዝ | | | | |
| | - የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት ማካሄድ | ዋናው መስሪያቤትና በሁሉም ቅርንጫፍ ፅህፈትቤቶች | 30 ደቂቃ | 400 | - የተሟላ ማመልከቻ<br>- ኦርጅናል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት<br>- በባለሥልጣኑ፣ ባለስልጣኑ በወከለው አካል ወይም በድርጅቱ ራሱ የተካሄደ የኢንስፔክሽን ሪፖርት |
| | - የቴክኒካል ባለሙያ/የባለቤትነት/ስም ለውጥ ለማድረግ | " | 30 ደቂቃ | 400 | - የተሟላ ማመልከቻ<br>- የቴክኒካል ባለሙያው የትምህርት ማስረጃና የቅጥር ስምምንት ውል<br>- የቴክኒካል ባለሙያው ሁለት ፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች |
| | - የጠፋ ወይም የተበላሸ ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር | " | 30 ደቂቃ | 400 | - የተሟላ ማመልከቻ<br>- የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የጠፋ ከሆነ ስለመጥፋቱ የፖሊስ ማረጋገጫ ደብዳቤ<br>- የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተበላሸ ከሆነ የተበላሸውን |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወረቀት መስጠት | | | | የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት<br>- የድርጅቱ ባለቤት፣ ቴክኒካል ማናጀር ወይም ስራስከያጅ ሁለት ፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች |
| | - የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መሰረዝ/መመለስ | " | 30 ደቂቃ | - | - የተጋላ ማመልከቻ<br>- በድርጅቱ ውስጥ በተለያየ ምክንያት ያልተሸጡ፣ የተበላሹ ወይም አገልግሎት ላይ የማይውሉ ምርቶች ካሉ የምርቶቹ ሁኔታ ዝርዝር መረጃና በቀጣይ በምን አግባብ እንደሚስተናገዱ የሚገልፅ መረጃ<br>- ኦርጅናል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ |

**ማብራርያ**

SRA -ጠንካራ ተቆጣጣሪ አካል ባለባቸው ሀገራት የሚመረቱና የዓለም ጤና ድርጅት እውቅና በሰጣቸው አምራቾች የሚመረቱ መድሀኒቶች
Non SRA - ጠንካራ ተቆጣጣሪ አካል በሌላቸው ሀገራት የሚመረቱና የዓለም ጤና ድርጅት እውቅና ያልሰጣቸው አምራቾች የሚመረቱ መድሀኒቶች
Fast truck


## 5.3የጤና ባለሙያዎች ሙያ ምዝገባና ፈቃድ መስጠት

### 5.3.1 የአገልግሎቱ መግለጫ

በዚህ አገልግሎት ውስጥ በአዋጅ ቁጥር 661/2002 መሰረት በፌዴራል ደረጃ ተመዝግበው የሙያ ፈቃድ የሚሰጣቸውና ቁጥጥር የሚደረግባቸው ጤና ባለሙያዎች ሙያዊ ብቃትና ስነ ምግባር በማረጋገጥ የመመዝገብና ወደ ስራ ለመግባት የሚያስችላቸው የሙያ ፈቃድ የሚሰጥበት ነው፡፡

የሙያ ፈቃድ ለመስጠት በዋናነት የጤና ባለሙያዎቹ የትምህርት ማስረጃዎችና ተያያዥ የሆኑ መረጃዎች በመገምገም ባለሙያው የተጣለበትን ሙያዊ ግዴታ ለመወጣት የሚያስችል ቁመና ያለው ስለመሆኑ ሲረጋገጥ ነው የሙያ ፈቃድ የሚሰጠው፡፡

### 5.3.2 የአገልገሎት አሰጣጥ ሂደት



## 5.3.3 አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ፣ የሚፈጀው ጊዜ፣ ተገልጋዮች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

| ተቁ | የሚሰጡ አገልገሎት ዝርዝር | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱ ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ | የአገልግሎት ክፍያ | አገልግሎቱ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አዲስ የጤና ባለሙያ የሙያ ፈቃድ መስጠት | በዋናው መስሪያቤትና ሁሉም ቅርንጫፍ ፅህፈትቤቶች | 45 ደቂቃ | 100 ብር | *የሀገር ውስጥ ጤና ባለሙያ*<br>- የተሟላ ማመልከቻ<br>- የትምህርት ማስረጃ ፣የጤና ምርመራ ሰርተፍኬትና የስራ ልምድ (በስራ ላይ ለቆዩ ባለሙያዎች)<br>- የወጭ መጋራት ላለባቸው ባለሙያዎች አገልግሎታቸውን ማጠናቀቃቸውን የሚገልፅ ከሚመለከተው አካል ደብዳቤ<br>- ሁለት ፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች<br>*ከውጭ ሀገር ለሚመጡ ባለሙያዎች*<br>- የተሟላ ማመልከቻ<br>- የትምህርት ማስረጃ፣ የሙያ ፈቃድና የስራ ልምድ፣የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ማስረጃ<br>- ሁለት ፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች እና<br>- ሌሎች በጤና ባለሙያዎች ምዝገባና ፈቃድ መመርያ ላይ የተጠቀሱ መስፈርቶች |
| 2. | ከውጭ ሀገር የሚመጡ የጤና ባለሙያዎች መመዝገብና የሙያ ፈቃድ መሰጠት | " | 45 ደቂቃ | 100 ዶላር | |
| 3. | የጤና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ አግባብነት መረጃ ማረጋገጥ | " | 15 ደቂቃ | 100 ዶላር | - የተሟላ ማመልከቻ ና ኦርጅናል የሙያ ፈቃድ |
| 4. | የመድሀኒት አስተዋዋቂ ባለሙያዎች ፈቃድ መስጠት | " | 40 ደቂቃ | | - የተሟላ ማመልከቻ<br>- የባለሙያው የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ፣<br>- ከዚህ በፊት ሲሰራበት ከነበረው ተkም የቅርብ ጊዜ/አንድ ወር ያላለፈው የስራ መልቀቂያ<br>- ከመድሀኒት ፋብሪካው ጋር የተገባ የስራ ስምምነት ውል<br>- የባለሙያው ሁለት ፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች |
| 5. | የሙያ ፈቃድ እድሳት ማካሄድ | " | 55 ደቂቃ | 50 ብር | - ቀድሞ የወሰዱት ኦርጅናል የሙያ ፈቃድ፣የስራ ልምድ<br>- የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ (CPD) ስልጠና መውሰዳቸውን ማረጋገጫ ማስረጃዎች |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | - ወቅታዊ የጤና ምርመራ ሰርተፍኬት<br>- ሁለት ፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች |
| 6. | በምግብና ጤና ላይ የማማከር አገልሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች የስራ ፈቃድ መስጠት | " | 40 ደቂቃ | 200 ብር | - የተጋላ ማመልከቻ<br>- የባለሙያው የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ፣<br>- የቤት ካርታ ኮፒ ወይም በሰነዶች ማረጋገጫ ፅህፈትቤት የተረጋገጠ የቤት ኪራይ ውል |


## 5.4የምግብና መድሀኒት ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ማካሄድ

### 5.4.1 የአገልግሎቱ መግለጫ

የምግብና መድሀኒት ጥራት ምርመራ አገልግሎት በዋናነት በባለስልጣን መስሪያቤቱ በተለያዩ ደረጃዎች በሚካሄዱ የቁጥጥር ስራዎች ላይ ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚውሉ ምርቶች ጥራትና ደህንነት ላይ ጥርጣሬ ሲኖር ናሙናዎች ተወስደው የሚመረመሩበትና ተገቢው መስፈርት ማሟላታቸው የሚረጋገጥበት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ ተገልጋዮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላትበላቦራቶሪውእንዲመረመርላቸው የሚፈልጉዋቸው ምግብና መድሀኒት ሲኖር በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት የምርመራ አገልግሎት የሚሰጥበት ነው፡፡

አገልግሎቱ በዋናነት የምግብና መድሀኒት ፊዚኮ ኬሚካል፣ ማይክሮ ባዮሎጂካልና ቶክሲኮሎጂካል ምርመራዎች ሲሆን የመድሀኒት ጥራት ምርመራ የሚካሄደው በዋናው መስሪያቤት በሚገኘው የመድሀኒት ላቦራቶሪ ሲሆን የምግብ ጥራት ምርመራ የሚካሄደው ደግሞ ፓስተር በሚገኘው የባለስልጣን መስሪያቤቱ የምግብ ጥራት ምርመራ ዳይሬክቶሬት ላይ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ውሱን የምርመራ አገልግሎቶች በአራት ቅርንጫፍ ፅህፈትቤቶች ይሰጣል፡፡

### 5.4.2 የአገልገሎት አሰጣጥ ሂደት




### 5.4.3 አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ፣ የሚፈጀው ጊዜ፣ ተገልጋዮች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

| ተቁ | የሚሰጡ አገልገሎት ዝርዝር | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱ ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ | የአገልግሎት ክፍያ | አገልግሎቱ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የምግብ ጥራትና ደህንነት ምርመራ ማካሄድ | | | | |
| | - ፊዚኮ ኬሚካል | በማእከላዊና የቅ/ፅ/ቤቶች ላቦራቶሪዎች | 15 ቀን 30 ደቂቃ | በሚንስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 370/2008 መሰረት | - የተሟላ ማመልከቻ<br>- በቂ የምርቱ ናሙና |
| | - ማይክሮባዮሎጂካል | | 15 ቀን 30 ደቂቃ | | |
| | - ቶክሲኮሎጂ | በማእከላዊ ላቦራቶሪ | 17 ቀን 30 ደቂቃ | | |
| 2. | የመድሀኒት፣ኮስሞቲክስና የላቦራቶሪ ኬሚካሎችና ሪኤጀንቶች ጥራት ምርመራ ማካሄድ | | | | |
| | - ፊዚኮ ኬሚካል | በማእከላዊና ቅ/ፅ/ቤቶች | 15 ቀን 30 ደቂቃ | | - የተሟላ ማመልከቻ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | - ማይክሮባዮሎጂካል | በማእከላዊ ላቦራቶሪ | 25 ቀን 30 ደቂቃ | | - በቂ የምርቱ ናሙና፣Test methods & Referwnce standard |
| | - **ኮንዶም ምርመራ ማካሄድ** | " | 4 ቀን 30 ደቂቃ | | |
| 3. | የህክምና መሳርያዎች ምርመራ ማካሄድ | " | 5 | | - የተሞላ ማመልከቻ<br>- በቂ የምርቱ ናሙና |


## 5.5በመግቢያና መውጫ ኬላዎች የመልቀቅያ ፈቃድ መስጠት

## 5.5.1 የአገልግሎቱ መግለጫ

ይህ አገልግሎት በዋናነት በሀገራችን ተመርተው ወደ ተለያዩ የውጭ ሀገራት የሚላኩና ውጭ ሀገር ተመርተው ወደሀገራችን የሚገቡ ምግቦች፣መድሀኒት፣የህክምና መሳርያዎችና መገልገያዎች፣ የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶችና የውበት መጠበቂያ ምርቶች ጥራትና ደህንነት በማረጋገጥ ወደ ውጭ ሀገር እንዲወጡ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የመውጫ ወይም መግቢያ መልቀቂያ ፈቃድ የሚሰጥበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአለማቀፍ ደረጃ የጤናና ኳራንታይን ቁጥጥር የሚካሄድባቸውመንገደኞች ከተላላፊ በሽታዎች ነፃ ስለመሆናቸው የሚረጋገጥበትና እንዲሁም የአስከሬንና ሌሎች የአውሮፕላን ርጭት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

ይህ አገልግሎት በሀገሪቱ በሚገኙ 17 የመውጫና መግቢያ ኬላዎች ይሰጣል፡፡

## 5.5.2 የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት



## 5.5.3 አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ፣ የሚፈጅው ጊዜ፣ ተገልጋዮች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

| ተቁ | የሚሰጡ አገልግሎት ዝርዝር | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱ ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ | የአገልግሎት ክፍያ ብር | አገልግሎቱ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የምግብ ጥራትና ደህንነት በማረጋገጥ የመልቀቂያ ፈቃድ መስጠት | | | | |
| 1.1 | - ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ምግብ | በሁሉም የመግቢያና መውጫ ኬላዎች | - 15 ቀን 50 ደቂቃ (with lab)<br>- 50 ደቂቃ (without lab) | 10 ብር በቶን | - የተሟላ ማመልከቻ<br>- ኢንቮይስ፣ፓኪንግ ሊስት፣ዲክለራስዮን፣የመጓጓዣ ሠነድ<br>- ሠርተፍኬት ኦፍ ኦሪጅን<br>- የጤና ሠርተፍኬት (ኦርጅናል)፣<br>- የፋይቶ ሳንተሪ ሠርተፍኬት እና ፋሙጌሽን ሰርተፊኬት/ተጨማሪ የምርት ሂደት ያልተካሄደባቸው የግብርና ምርቶች/<br>- የቬተርነሪ ሠርተፊኬት /ለእንስሳት ተዋፆኦ/<br>- የ3ኛ ወገን የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ወረቀት (የ3ኛ ወገን ማረጋገጫ ለሚያስፈልጋቸው ምግቦች)<br>- የምርት ፍተሻ ኢንስፔክሽን ሪፖርት (በባለስልጣኑ ኢንስፔክተሮች የሚካሄድ)<br>እና<br>- ሌሎች በበምግብ አስመጪ፣ላኪና አከፋፋይ ቁጥጥር መመርያ ላይ የተጠቀሱ መስፈርቶች |
| 1.2 | - ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ የምግብ ጥሬ እቃ | " | 50 ደቂቃ | 10 ብር በቶን | - የተሟላ ማመልከቻ<br>- ኢንቮይስ፣ፓኪንግ ሊስት፣ዲክለራስዮን፣የመጓጓዣ ሠነድ<br>- የጤና ሠርተፍኬት (ኦርጅናል)<br>- ሴፍቲ ዳታ ሺት(safety data sheet for food grade chemicals)<br>- ሠርተፍኬት ኦፍ ኦሪጅን<br>እና<br>ሌሎች በበምግብ አስመጪ፣ላኪና አከፋፋይ ቁጥጥር መመርያ ላይ የተጠቀሱ መስፈርቶች |
| 1.3 | - ወደ ውጭ ሀገር ለሚላክ ምግብ | " | 30 ደቂቃ | 4.50 በቶን | - የተሟላ ማመልከቻ<br>- በመመርያው መሰረት ተመርቶ የታሸገ ምግብ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የጤናማነት ማረጋጫ ምስክር ወረቀት መስጠት | | | | - ፓኪንግ ሊስት፣ኮመርሻል ኢንቮይስ<br>- ፋይቶ ሰንታሪ( ለጥራጥሬ)፣ ቬተርነሪ ሠርተፊኬት /ለእንስሳት ተዋፆኦ/ እና<br>- ሌሎች በምግብ አስመጪ፣ላኪና አከፋፋይ ቁጥጥር መመርያ ላይ የተጠቀሱ መስፈርቶች |
| 2. | **የመድሀኒትና የህክምና መገልገያዎች ጥራት በማረጋገጥ የመልቀቂያ ፈቃድ መስጠት** | | | | |
| 2.1 | ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ መድሀኒትና የህክምና መገልገያዎች | " | - 30 ቀን 1 ሰዓት ከ 5 ደቂቃ ((with lab)<br>- 1ሰዓት ከ 5 ደቂቃ (without lab) | 350 | - የተሞላ ማመልከቻ<br>- የምርቱ ምዝገባ ሠርተፍኬት ኮፒ<br>- ወቅታዊ የቅድመ ማስገቢያ ፍቃድ (9 ወር ያልበለጠ)/<br>- ልዩ የማስገቢያ ፈቃድ ለናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሀኒቶችና ኬሚካች<br>- የባች ምርመራ ሠርተፊኬት (COA)<br>- ኢንቮይስ/፣ዲክላራስዮን፣ፓክንግ ሊስት/፣የመጓጓዥ ሠነድ/AWB/BL/TWB<br>- ሠርተፍኬት ኦፍ አርጅን<br>- የምርት ፍተሻ ኢንስፔክሽን ሪፖርት (በባለስልጣኑ ኢንስፔክተሮች የሚካሄድ) እና<br>- ሌሎች በመድሀኒትና ህክምና መሳርያዎች አስመጪ፣ላኪና አከፋፋይ ቁጥጥር መመርያ ላይ የተጠቀሱ መስፈርቶች |
| 2.2 | ወደ ውጭ ሀገር ለሚላክ መድሀኒትና የህክምና መገልገያዎች የጤናማነት ማረጋጫ ምስክር ወረቀት መስጠት | " | 40 ደቂቃ | 150 | - የተሞላ ማመልከቻ<br>- የምርቱ ምዝገባ ሠርተፍኬት ኮፒ<br>- በአግባቡ ታሽጎ የቀረበ ምርት<br>- ኢንቮይስና ፓኪንግ ሊስት |
| 3. | **የህክምና መሳርያዎችና የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶች ጥራት በማረጋገጥ የመልቀቂያ ፈቃድ መስጠት** | | | | |
| 2.3 | - ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የህክምና መሳርያዎችና የላባራቶሪ ሪኤጀንቶች | " | 5 ቀን 50 ደቂቃ (with lab)<br>50 ደቂቃ (without lab) | 350 | - የተሞላ ማመልከቻ<br>- የምርቱ ምዝገባ ሠርተፍኬት ኮፒ<br>- ወቅታዊ የቅድመ ማስገቢያ ፍቃድ (9 ወር ያልበለጠ)/የባች ምርመራ ሠርተፊኬት( for sterile only)<br>- ኮሜርሻል ኢንቮይስ/፣ዲክላራስዮን፣ፓክንግ ሊስት/፣የመጓጓዥ ሠነድ/<br>- ሠርተፍኬት ኦፍ አሪጅን |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | - የምርት ፍተሻ ኢንስፔክሽን ሪፖርት (በባለስልጣኑ ኢንስፔክተሮች የሚካሄድ)<br>እና<br>- ሌሎች በመድሀኒትና ህክምና መሳርያዎች አስመጪ፣ላኪና አከፋፋይ ቁጥጥር መመርያ ላይ የተጠቀሱ መስፈርቶች |
| 2.4 | - ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ የህክምና መሳርያዎችና የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶች የጤናማነት ማረጋጫ ምስክር ወረቀት መስጠት | " | 40 ደቂቃ | 150 | - የተጠላ ማመልከቻ<br>- የምርቱ ምዝገባ ሠርተፍኬት ኮፒ<br>- በአግባቡ ታሽጎ የቀረበ ምርት<br>- ኢንቮይስና ፓኪንግ ሊስት |
| 4. | **የውበት መጠበቂያምርቶችና ንጽህና መጠበቅያ ዲተርጀንቶ ጥራት በማረጋገጥ የመልቀቂያ ፈቃድ መስጠት** | | | | |
| 3.1 | - ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የውበት መጠበቂያ ምርቶችና ንጽህና መጠበቅያ ዲተርጀንቶ | " | 15 ቀን 50 ደቂቃ | 350 | - የተጠላ ማመልከቻ<br>- የምርቱ ምዝገባ ሠርተፍኬት ኮፒ<br>- የባች ምርመራ ሠርተፊኬት<br>- ኢንቮይስ፣ዲክላራስዮን፣ፓክንግ ሊስት/፣የመጓጓዥ ሠነድ/<br>- ሠርተፍኬት ኦፍ ኦሪጅን<br>- የምርት ፍተሻ ኢንስፔክሽን ሪፖርት (በባለስልጣኑ ኢንስፔክተሮች የሚካሄድ)<br>እና<br>- ሌሎች በኮስሞቲክስ አስመጪ፣ላኪና አከፋፋይ ቁጥጥር መመርያ ላይ የተጠቀሱ መስፈርቶች |
| 3.2 | - ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ የውበት መጠበቂያ ምርቶችና ንጽህና መጠበቅያ ዲተርጀንቶ | " | 40 ደቂቃ | 150 | - የተጠላ ማመልከቻ<br>- የምርቱ ምዝገባ ሠርተፍኬት ኮፒ<br>- በአግባቡ ታሽጎ የቀረበ ምርት<br>- ኢንቮይስና ፓኪንግ ሊስት |
| 5. | የመድሀኒት፣ላቦራቶሪ ሪኤጀንቶችና የውበት መጠበቂያ ምርቶች ጥሬ እቃ ግብአት ጥራት በማረጋገጥ የመልቀቂያ ፈቃድ መስጠት | " | 40 ደቂቃ | 350 | - የተጠላ ማመልከቻ<br>- ወቅታዊ ቅድመ ፍቃድ (9 ወር ያልበለጠ)/<br>- ሴፍቲ ዳታ ሺት /chemical safety data sheet/<br>- ኮሜርሻል ኢንቮይስ/፣ዲክላራስዮን፣ፓክንግ ሊስት/፣የመጓጓዥ ሠነድ/<br>- ሠርተፍኬት ኦፍ ኦሪጅን<br>- የምርት ፍተሻ ኢንስፔክሽን ሪፖርት (በባለስልጣኑ ኢንስፔክተሮች የሚካሄድ) |
| 6. | **የትምባሆ ገላጭ ፅሁፍ አግባብነት በማረጋገጥ የመልቀቅያ ፈቃድ መስጠት** | | | | |


| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 3.3 | - ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ትምባሆ | " | 40 ደቂቃ | 700 | - የተቋላ ማመልከቻ<br>- ኮሜርሻል ኢንቮይስ/፣ዲክላራስዮን፣ፓክንግ ሊስት/፣የመጓጓዥ ሠነድ/<br>- ሠርተፍኬት ኦፍ አሪጅን<br>- የምርት ፍተሻ ኢንስፔክሽን ሪፖርት (በባለስልጣኑ ኢንስፔክተሮች የሚካሄድ) |
| 3.4 | - ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ ትምባሆ | " | 40 ደቂቃ | 300 | - የተቋላ ማመልከቻ<br>- በአግባቡ ታሽጎ የቀረበ ምርት ኢንቮይስና ፓኪንግ ሊስት |
| 7. | በአስከሬን ላይ የተላላፊ በሽታዎች ኢንስፔክሽን በማካሄድ የመልቀቂያ ፈቃድ መስጠት | " | 25 ደቂቃ | - | - የተቋላ ማመልከቻ<br>- የአስከሬን ምርመራ ምስክር ወረቀት |
| 8. | በአውሮፕላን ላይ የተላላፊ በሽታዎችና ነብሳት ቁጥጥር በማካሄድ የርጭት ሰርተፊኬት መስጠት | ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፍያ ላይ ባላቸው ኬላዎች | 35 ደቂቃ | 350 | - የተቋላ ማመልከቻ<br>- የአውሮፕላኑ የጉዞ ሰነድ |

## 5.6አገልግሎት ላይ የማይውሉ ምርቶች በአግባቡ መወገዳቸውን ማረጋገጥ

### 5.6.1 የአገልግሎቱ መግለጫ

ይህ አገልግሎት በሀገሪቱ ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው እንዲሁም በአመራረት፣ አከመቻቸትና ማ11ዝ ሂደት ላይ በተለያየ ምክንያት ምርቶቹ ለተለያዩ የጥራትና ደህንነት መ1ደል ሲጋለጡና ለምግብነት አገልግሎት የማይውሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ በአከባቢ፣ በሰውና እንስሳት ጤና ላይ ጉዳት በማያስከትል ቦታ በአግባቡ እንዲወገዱ የማድረግና ይህም ስለመደረጉ የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለባለ ንብረቱ የመስጠት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

### 5.6.2 የአገልገሎት አሰጣጥ ሂደት




## 5.6.3 አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ፣ የሚፈጀው ጊዜ፣ ተገልጋዮች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

| ተ ቁ | የሚሰጡ አገልገሎት ዝርዝር | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱ ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ | የአገልግሎት ክፍያ | አገልግሎቱ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አገልግሎት ላይ የማይውሉ ምርቶች በአከባቢ፣ በሰውና በእንስሳት ጤና ላይ ጉዳይ እንዳያስከትሉ አግባበ መወገዳቸውን ማረጋገጥ | በዋናው መስሪያቤት ፣ ሁሉም ቅርንጫፍ ፅህፈትቤቶችና የመውጫና መግቢያ ኬላዎች | 1 ወር | 1450 | - የተሟላ ማመልከቻ<br>- የሚወገዱ ምርቶች ዝርዝር<br>- ተገቢ የማስወገጃ ቦታ ማዘጋጀት |


<u>ማሳሰብያ</u>- የተቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ በአንድ ቀን ውስጥ ለሚሰራ ስራ ብቻ ሲሆን ስራውን ከአንድ ቀን በላይ ከወሰደ ባለሙያዎቹ በቆዩበት ቀን ተሰልቶ የአበል ክፍያ ተጨማሪ የሚታሰብ ይሆናል፡፡

## 5.7የመረጃ አቅርቦት ጥያቄ ምላሽ መስጠት

### 5.7.1 የአገልግሎቱ መግለጫ

ባለስልጣን መስሪያቤቱ የሚሰጣቸው አገልግሎት፣ የሚያከናውናቸው የቁጥጥር ስራዎች፣ የተወሰዱ እርምጃዎች፣ የስራ አፈፃፀም ሪፖርቶች እና የመሳሰሉ መረጃዎች ከተገልጋዮች፣ባለድርሻ አካላት፣ የሚድያ ተkማት፣ ተመራማሪዎች፣ ፖሊሲ አውጪዎች፣ ዓለም አቀፍ ተkማት እና ሌሎች መረጃ የሚፈልጉ አካላት ጥያቄ ሲቀርብ ጥራቱን የጠበቀ መረጃ በወቅቱ የሚሰጥበት ነው፡፡

### 5.7.2 የአገልገሎት አሰጣጥ ሂደት




### 5.7.3 አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ፣ የሚፈጀው ጊዜ፣ ተገልጋዮች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች


| ተቁ | የሚሰጡ አገልገሎት | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱ ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ | አገልግሎቱ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ለሚጠየቁ ወቅታዊ መረጃዎች ጥያቄ ምላሽ መስጠት | በዋናው መስሪያቤትና ሁሉም ቅርንጫፎች | 1 ቀን | ምንም አያስፈልግም |

## 5.8ከህብረተሰቡና ሌሎች አካላት የሚመጡ ጥቆማዎች ምላሽ መስጠት

### 5.8.1 የአገልግሎቱ መግለጫ

ይህ አገልግሎት ከህገወጥ ምግብና መድሀኒት ንግድና ጤና አገልግሎት ስራዎች እንዲሁም ሌሎች ህጉ ከሚፈቅደው ውጪ የሚከናወኑ ተግባራት ሲኖሩና በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ህብረተሰቡ ወይም ሌሎች አካላት በአካል፣በ8482 ነፃ የስልክ መስመር እንዲሁም ሌሎች የጥቆማ ማቅረበያ መንገዶች ጥቆማ የሚቀርብበትና በጉዳዩ ላይ ተገቢው ምርመራ በማካሄድ የተወሰደው እርምጃ ለጥቆማ አቅራቢው አካል ምላሽ የሚሰጥበት ነው፡፡

### 5.8.2 የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት




### 5.8.3 አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ፣ የሚፈጀው ጊዜ፣ ተገልጋዮች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

| ተቁ | የሚሰጡ አገልገሎት ዝርዝር | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱ ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ | አገልግሎቱ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የሚቀርበው ጥቆማ አጣርቶ ምላሽ መስጠት | በዋናው መስሪያቤትና በሁሉም ቅርንጫፍ ፅህፈትቤቶች | 16 ቀን 1 ሰዓት 10 ደቂቃ | - በማስረጃ የተደገፈ መረጃ |


## 5.9ከተገልጋዮችና አገልግሎት ተጠቃሚ አካላት የሚነሳ ቅሬታ ምላሽ መስጠት

| ተቁ | የሚሰጡ አገልገሎት ዝርዝር | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱ ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ | አገልግሎቱ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች |
|---|---|---|---|---|
| 2. | ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር የሚቀርብ ቅሬታ ምላሽ መስጠት | በዋናው መስሪቤት፣ ቅርንጫፍ ፅህፈትቤቶችና የመግቢያና መውጫ ኬላዎች | 5 ቀን 10 ደቂቃ | - የተሟላ ማመልከቻ<br>- ቅሬታ የቀረበበትን ጉዳይ በተመለከተ ዝርዝር የፅሁፍ መረጃ<br>- ቅሬታ የቀረበበት የስራ ክፍል ወይም ባለሙያ ስም<br>- በባለሙያው ወይም ስራ ክፍሉ የተሰጣቸው የመጨረሻ ውሳኔ |
| 3. | ከአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ አግባብነት ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ቅሬታ ምላሽ መስጠት | | 1 ወር 1 ቀን 10 ደቂቃ | - የቅሬታው ዝርዝር መግለጫ የያዘ ማመልከቻ<br>- የተሰጣቸው የውሳኔ ደብዳቤ ኮፒ<br>- ስለ ጉዳዩ በተመለከተ ሊያስረዱ የሚችሉ አጋዥ መረጃዎች |
| 4. | ከሙያ ስነ ምግባርና ብቃት ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ቅሬታ ምላሽ መስጠት | | 3 ወር 1 ቀን 10 ደቂቃ | - የተሟላ ማመልከቻ<br>- የተበዳይና በደል ያደረሰው ጤና ባለሙያ ስምና የሚሰራበት ተkም አድራሻ<br>- ቅሬታ የቀረበበትን ጉዳይ በተመለከተ ዝርዝር የፅሁፍ መረጃ<br>- ስለ ተፈጠረው የህክምና ስህተት የሚገልፅ አጋዥ መረጃዎች |

## 6. የቅሬታ አቀራረብና ግብረመልስ አሰጣጥ ስርዓታችን

ማንኛውም ተገልጋይ በአገልግሎት አሰጣጣችን ሂደት ማንኛውም ዓይነት ቅሬታ ሲኖረው ቅሬታውን በፅሁፍ የማቅረብና ለአቀረበው ቅሬታ ምላሽ የማግኘት መብት አለው፡፡

በዚህ መሰረት ቅሬታውን ከዚህ በታች በተገለፀው አግባብ መሰረት ማቅረብ ይችላል፡፡




በየደረጃው ያለ ፈፃሚ ወይም አመራር ከተገልጋዮች የሚቀርብለትን ቅሬታ አግባብነት በመመርመር 24 ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

ቅሬታ አቅራቢው በየደረጃው ባለ ፈፃሚና አመራር የተሰጠ ውሳኔ ካላረካውና እስከ በላይ ሀላፊዎች ድረስ የሚሄድ ከሆነ የመስሪያቤቱ የበላይ ሀላፊዎች ከ5 ቀን ባልበለጠ ጊዜ የመስሪያቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡ በዚህ ካልረካ የሀገሪቱ የፍትህ ስርዓት ተከትሎ ወደ ፍርድቤት ሊሄድ ይችላል፡፡

ማንኛውም ዓይነት ቅሬታ ሲቀርብም ሆነ ምላሽ ሲሰጥ በፅሁፍ ይሆናል፡፡

## 7. ተጨማሪ የመረጃ ምንጮቻችን

በባለስልጣንመስሪያቤታችን ስለምንሰጣቸው አገልግሎቶች፣የምናከናውናቸው የቁጥጥር ስራዎች፣ አዳዲስ የህግ ማእቀፎችና ሌሎች ወቅታዊ ጠቃሚ ተጨማሪ መረጃዎች

- በwww.fmhaca.gov.et ድህረገፃችን
- በHealth port የሞባይል አፕሊኬሽናችን እና
- በ8482 ነፃ የስልክ መስመራችን ማግኘት ይችላሉ፡፡

## 8. የተkሙ የበላይ ሀላፊዎችና የአገልግሎት መስጫ ቦታዎች አድራሻ

በተkማችን ውስጥ በምንሰጣቸው አገልግሎቶችና በምናከናውናቸው የቁጥጥር ስራዎች በአሰራራችንም ሆነ በአገልግሎት ሰጪና ተቆጣጣሪ ባለሙያዎቻችን ማንኛውም ዓይነት አስተያየት ወይም ቅሬታ ካልዎት በሚከተሉት የተkማችን የበላይ ሀላፊዎችአድራሻ በቀጥታ በመደወል ወይም በአካል በመገኘት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

| ተቁ | የሀላፊዎች ስም | ሀላፊነት | ስልክ | ኢ-ማይል |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ የሁሉ ደነቀው | ዋና ዳይሬክተር | | |
| 2. | ወሪት ሄራን ገርባ | ኢንስፔክሽንና ፈቃድ ም/ዋና ዳይሬክተር | | |
| 3. | ደ/ር ኬረዲን | ም/ዋና ዳይሬክተር | | |
| 4. | አቶ በቂላ ባይሳ | የምግብና መድሀኒት ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ም/ዋና ዳይሬክተር | | |
| 5. | አቶ መሓሪ ብርሃነ | የዋና ዳይሬክተር ፅ/ቤት ሃላፊ | | |

# 9. የዋናው መሰሪያቤታችን ፣ቅርንጫፍ ፅህፈትቤቶቻችንና የመውጫና መግቢያ ኬላዎቻችን አድራሻዎች

| ተቁ | የመስሪያቤቱ ስም | አድራሻ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል | ከተማ | የቦታው ልዩ መጠርያ | ስልክ | ፋክስ | ኢሜይል |
| 1. | **ዋናው መሰሪያቤት** | አዲስ አበባ | አዲስ አበባ | ቦሌ መንገድ ከቦሌ ማተሚያ አለፍ ብሎ | | | |
| 2. | **ማእከላዊ ኢትዮጵያ ቅ/ፅ/ቤት** | አዲስ አበባ | አዲስ አበባ | ዋናው መስሪያቤት ውስጥ | | | |
| | በስሩ የሚገኙ የመውጫና መግቢያ ኬላዎች | | | | | | |
| | ▪ ካርጎ | አዲስ አበባ | አዲስ አበባ | ቦሌ ዓለም አቀፍ አየርፖርት ካርጎ ተርሚናል | | | |
| | ▪ ቦሌ ዓለም አቀፍ አየርፖርት ተርሚናል | አዲስ አበባ | አዲስ አበባ | ተርሚናል 1 እና 2 | | | |
| | ▪ ቃሊቲ | አዲስ አበባ | አዲስ አበባ | ቃሊቲ ባቡር ጣብያ | | | |
| | ▪ ሞጆ ደረቅ ወደብ | ኦሮሚያ | ሞጆ | ሞ ደረቅ ወደብ ውስጥ | | | |
| | ▪ አዳማ | ኦሮምያ | አዳማ | | | | |
| | ▪ ገላን | ኦሮሚያ | ገለን | ገላን ደረቅ ወደብ ውስጥ | | | |
| 3. | **ምስራቅ ኢትዮጵያ ቅ/ፅ/ቤት** | ድሬዳዋ | ድሬዳዋ | የድሬዳዋ ከተማ ቁራ አጠገብ | | | |
| | በስሩ የሚገኙ የመውጫና መግቢያ ኬላዎች | | | | | | |
| | ▪ ድሬዳዋ | ድሬዳዋ | ድሬዳዋ | የድሬዳዋ ጉምሩክ ያለበት ግቢ ውስጥ | | | |
| | ▪ ድሬዳዋ ዓለማቀፍ አየርፖርት | ድሬዳዋ | ድሬዳዋ | ድሬዳዋ አየር ፖርት ግቢ ውስጥ | | | |
| | ▪ ደወሌ | ሱማሌ | ደወሌ | ደወሌ ከተማ | | | |
| | ▪ ጅጅጋ | ሱማሌ | ጅጅጋ | ጉምሩክ ፅህፈትቤት ቅጥር ግቢ | | | |
| | ▪ ተጎ ውጫሌ | ሱማሌ | ተጎ ውጫሌ | | | | |
| 4. | **ደቡብ ኢትዮጵያ ቅ/ፅ/ቤት** | ደቡብ | ሀዋሳ | | | | |
| | በስሩ የሚገኙ የመውጫና መግቢያ ኬላዎች | | | | | | |
| | ▪ ሞያሌ | ኦሮሚያ | ሞያሌ | ከጉምሩክ ፅህፈትቤት ወረድ ብሎ | | | |
| 5. | **ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቅ/ፅ/ቤት** | ኦሮምያ | ጅማ | ጅማ ከተማ | | | |
| 6. | **ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ቅ/ፅ/ቤት** | አማራ | ባህርዳር | የአማራ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን አጠገብ | | | |
| | በስሩ የሚገኙ የመውጫና መግቢያ ኬላዎች | | | | | | |
| | ▪ ግንቦት 20 ዓለማቀፍ አየርፖርት | አማራ | ባህርዳር | ግንቦት 20 አየርፖርት ግቢ ውስጥ | | | |
| | ▪ መተማ | አማራ | መተማ | መተማ ከተማ | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የወሃንስ | | | | |
| 7. | **ሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ ቅ/ፅ/ቤት** | አማራ | ኮምቦልቻ | | | | |
| | በስሩ የሚገኙ የመውጫና መግቢያ ኬላዎች | | | | | | |
| | ▪ ኮምቦልቻ | አማራ | ኮምቦልቻ | | | | |
| | ▪ ሰመራ | አፋር | ሰመራ | ሰመራ ደረቅ ወደብ ውስጥ | | | |
| | ▪ ጋላፊ | አፋር | ጋላፊ | ጉምሩክ ፅህፈትቤት ቅጥር ግቢ | | | |
| 8. | **ሰሜን ኢትዮጵያ ቅ/ፅ/ቤት** | ትግራይ | መቐለ | የክልሉ ጤና ቢሮ ፊትለፊት | | | |
| | በስሩ የሚገኙ የመውጫና መግቢያ ኬላዎች | | | | | | |
| | ▪ አሉላ አባነጋ ዓለማቀፍ አየርፖርት | ትግራይ | መቐለ | አሉላ አባነጋ አየርፖርት ግቢ ውስጥ | | | |
| | ▪ መቐለ ደረቅ ወደብ | ትግራይ | መቐለ | መቐለ ደረቅ ወደብ ውስጥ | | | |
| | ▪ ሁመራ | ትግራይ | ሁመራ | ደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ ህንፃ ውስጥ | | | |

# 10. የአገልግሎት መጠየቂያ ማመልከቻ ቅፆች